# የኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ ፣ወላይታ፣ጋሞ፣ ጌዴኦ እና ጎፋ እንዲሁም ቡርጂ፣ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ዲራሼ ልዩ ወረዳዎች በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ ሕዝበ ውሳኔ አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 19/2015 ዓ.ም

## ምዕራፍ አንድ

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተቋሙን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7/1/ እና /11/ እንዲሁም የኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት በቁጥር ፌደም/አፈ 15/80 ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በ6 ዞኖች እና በ5 ልዩ ወረዳዎች በአንድ የጋራ ክልል ሆኖ ለመደራጀት የተጠየቀውን ህዝበ ውሳኔ ለማስፈፀም ይህን የሕዝበ ውሣኔ አፈፃፀም መመሪያ አዉጥቷል።

**አንቀጽ 2. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ መመሪያ የኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ ፣ወላይታ፣ጋሞ፣ ጌዴኦ እና ጎፋ እንዲሁም ቡርጂ፣ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ዲራሼ ልዩ ወረዳዎች *በአንድ የጋራ ክልል በመሆን የመደራጀት ጥያቄ ሕዝበ ውሳኔ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 19/2015 ዓ.ም*" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 3. <u>ትርጓሜ</u>**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።
2) **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3) **"ህዝበ ውሳኔ"** ማለት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ወይም አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት ወይም የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ የሚደረግ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ነው።
4) የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በአዋጁ ላይ የተካተቱት የቃላትና ሐረጋት ትርጓሜዎች እንደ አግባብነታቸው ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ።

**አንቀጽ 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ የህዝበ ውሳኔ አፈጻጸም መመሪያ በኮንሶ፣ በደቡብ ኦሞ ፣በወላይታ፣በጋሞ፣ በጌዴኦ እና በጎፋ እንዲሁም በቡርጂ፣በባስኬቶ፣ በአሌ፣ በአማሮ እና በዲራሼ ልዩ ወረዳዎች በአንድ የጋራ ክልልነት የመደራጀት ጥያቄን በተመለከተ በዞኖቹ እና ልዩ ወረዳዎቹ የሚኖሩትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ውሳኔ ለማወቅ በሚደረግ ህዝበ ውሳኔ ሂደት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 5. <u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ መመሪያ በአንደኛው ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል።

**አንቀጽ 6. <u>ዓላማ</u>**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ ፣ወላይታ፣ጋሞ፣ ጌዴኦ እና ጎፋ እንዲሁም ቡርጂ፣ባስኬቶ፣ አሌ፣ አማሮ እና ዲራሼ ልዩ ወረዳዎች የሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በጋራ በአንድ ክልል የመደራጀት ውሳኔ ለማወቅ በሚደረገው ህዝበ ውሳኔ ሂደት ፦

1. የህዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎችን አወቃቀር፣ አደረጃጀትና ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መደንገግ ፤
2. በየደረጃው የሚመደቡ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ግልጽ፣ ፍትሐዊ፣እውነተኛና ነጻ ህዝበ ውሳኔ በገለልተኝነት እንዲያካሂዱ ማስቻል፤
3. የሕዝበ ውሳኔ ጥያቄውን ያቀረቡ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች አባላት ያለ ምንም አድሎ እና ችግር በሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ውጤታማ የመራጮች ምዝገባ ብሎም ውሳኔያቸውን በሚገባ የሚገልፁበት የድምፅ አሰጣጥ አሰራር መዘርጋት፤
4. የህዝበ ውሳኔው የመራጮች ምዝገባ፣ ድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና የውጤት አገላለጽ ሂደት ግልጽ ፣ ቀልጣፋ፣በአገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ ህጎች ተቀባይነት ያላቸውን መስፈርት ያሟላ እንዲሆን ማድረግ ናቸው።

# ምዕራፍ ሁለት

## <u>የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ አደረጃጀትና የቦርዱ ኃላፊነቶች</u>

### አንቀጽ 7. <u>የቦርዱ ተግባር እና ኃላፊነት</u>

1. የህዝበ ውሳኔውን የሚያስፈጽሙ ተአማኒ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸውን የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች በአዋጅ ቀጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(15) በተደነገገው መሰረት ፆታዊ ተዋፅኦን ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መልምሎ እና አሰልጥኖ ያሰማራል፤

2. የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ተግባራቸውን በብቃት እንዲወጡ ህዝበ ውሳኔ በሚካሄድባቸው ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ለሚቋቋሙ የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች አስተባባሪዎች ይመድባል፤

3. ለህዝበ ውሳኔ የሚያገለግሉ ሰነድና ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ ያዘጋጃል፤ በጥንቃቄ ወደ ዞን እና ልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች እና ምርጫ ጣቢያዎች በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤

4. ለህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ የጊዜ ሰሌዳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤ ለህዝብም ይፋ ያደርጋል፤

5. ህዝበ ውሳኔውን የሚመለከቱ የቅስቀሳ አይነቶችን፣ ይዘት እንዲሁም የጊዜ ሰሌዳ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤ለህዝብም ይፋ ያደርጋል፤

6. የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ የምርጫ ህጉ እና ቦርዱ ባወጣቸው መመሪያዎች መሰረት በሰላማዊነት፣ በፍትሃዊነት፣በታዓማኒና፣ያለአድልዎና በግልጽ መፈጸሙን ያረጋግጣል፤

7. ለህዝበ ውሳኔው አስፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት አስፈላጊው ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤

8. ከህዝበ ውሳኔው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

9. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ለህዝበ ውሳኔው የቀረቡትን አማራጭ ሃሳቦችን በማያሻማና ግልፅ በሆነ ሁኔታ በጽሁፍ ያሰፍራል፤

10. ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ለህዝበ ውሳኔ የቀረቡትን አማራጮች ምልክት ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። በጊዜ ገደቡ ውስጥ የማያመጡ ከሆነ ቦርዱ የምርጫ ምልክትን የሚገዙ ህጎች የሚደነግጉትን መስፈርት የሚያሟሉ ምልክቶችን ለህዝበ ውሳኔ ጥያቄው ለቀረቡት አማራጮች ይመርጣል፣ለህዝብም ይፋ ያደርጋል፤

11. ለህዝበ ውሳኔው ምርጫ ድምፅ መስጫነት የሚሆኑ ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ ነፍሰጡር ሴቶች እንዲሁም ሌሎች ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ታሳቢ ያደረጉ ምቹ በታዎችን እንዲዘጋጁ ጥረት ያደርጋል፤

12. በአዋጁ አንቀፅ 15/7/ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ የምርጫ ጣቢያ የሚስተናገደውን የመራጭ ብዛት ይወስናል፣ለህዝብም በይፋ ያሳውቃል፤

13. የመራጮች ትምህርት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

14. የህዝበ ውሳኔውን ምርጫ ለሚታዘቡ የአገር ውስጥ የሲቪል ማህበራት ታዛቢዎች በህግ አግባብ የታዛቢነት ፍቃድ ይሰጣል። በየደረጃውም የታዛቢዎች ስራ እንዲቀላጠፍ አስፈላጊውን ዕገዛ ያደርጋል፤

15. ህዝበ ውሳኔውን ለመዘገብ ለሚፈልጉ የመገናኛ ብዙኃን አግባብነት ባለው መመሪያ መሰረት ፍቃድ ይሰጣል፤

16. የህዝበ ውሳኔውን ውጤቶችን አረጋግጦ በህጉ መሰረት ይፋ ያደርጋል፤

17. የህዝበ ውሳኔው የመጨረሻ ውጤቶች እና የአፈፃፀም ሪፖርት አጠቃሎ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፤ ጥያቄውን ላቀረቡት የዞን እና የልዩ ወረዳ ምክር ቤቶችም ውጤቶች ያሳውቃል፤

18. በህዝበ ውሳኔው ሂደትና ውጤቶች በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አዋጁን እና የቅሬታ አቀራረብና አፈታት መመሪያውን መሰረት በማድረግ እንደ ጉዳዩ አግባብነት ተገቢውን የቅሬታ አፈታት መዋቅር እና አደረጃጀት በመዘርጋት እልባት እንዲያገኙ ያደርጋል፣

19. አግባብነት ባላቸው ህጎችና መመሪያዎች ላይ የተዘረዘሩ ሌሎች ለህዝበ ውሳኔው ውጤታማ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትና ኃላፊነቶች መፈፀም።

**አንቀጽ 8. <u>የሕዝበ ውሳኔ ጽሕፈት ቤቶች አደረጃጀት</u>**

በ6ቱ ዞኖችና በ5ቱ ልዩ ወረዳዎች የሚደረገውን ሕዝበ ውሳኔ በውጤታማነት ለማስፈፀም ቦርዱ የሚከተሉትን ጽህፈት ቤቶች ያደራጃል።

1. ህዝበ ውሳኔውን የሚያስተባብሩና ቁጥሩ በቦርዱ የሚወሰን አስፈፃሚዎች የሚኖሩት አንድ ዋና ማስተባበሪያ ፅ/ቤት እና በየዞኑ እና በልዩ ወረዳዎቹ ደረጃ የሚቋቋም ህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ያደራጃል፤
2. በተመረጡ የዞን ወይም ልዩ ወረዳዎች በማስተባበሪያነት የሚያገለግሉ ማዕከላት ያደራጃል፤
3. ቁጥሩ እንደ የሁኔታው በቦርዱ የሚወሰን ሆኖ የሕዝበ ውሣኔ አስፈፃሚዎች ያሉት የምርጫ ጣቢያዎችን ያቋቁማል።

# ምዕራፍ ሶስት

## <u>በህዝበ ውሳኔ ምርጫ ላይ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላት ተግባርና ሀላፊነት</u>

### አንቀጽ 9. <u>የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች ምልመላ</u>

1. ቦርዱ በየደረጃው ህዝበ ውሳኔውን በገለልተኛነት እና በታማኝነት የሚያስፈጽሙ የፆታን ተዋፅኦ መሰረት ባደረገ መልኩ አስፈፃሚዎችን ይመለምላል፡፡ በዚህ መሰረት አስፈጻሚዎቹ፡-
   ሀ/ ኢትዮጵያዊ የሆነ/ች፣
   ለ/ ዕድሜው/ዋ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ/የሆነች
   ሐ/ ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈፀም የሚሰጠውን ስልጠና ለመረዳት እና በዚህና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መመሪያዎች መሰረት የሚሰጣትን ሀላፊነት ለመፈጸም የሚያስችል የትምህርት ዝግጅት ያለው/ያላት
   መ/ የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ/ች መሆኑን ይረጋገጣል፡፡
2. ቦርዱ የሕዝበ ውሣኔ አስፈፃሚዎች ተግባራቸውን በገለልተኛነት፣ በታማኝነት እና በብቃት እንዲወጡ አስፈላጊውን ሥልጠና ይሰጣል፤ በየምርጫ ጣቢያዎች ያሰማራል፤
3. ህዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎች ኃላፊነታቸውን በገለልተኛነት፥ በቅንነት፥ በብቃት እና በታማኝነት መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የሥነ ምግባር ግዴታ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡

### አንቀጽ 10. <u>የህዝበ ውሳኔው ማስተባበሪያ ዋና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ዋና ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. በ6ቱ ዞኖችና በ5ቱ ልዩ ወረዳዎች የሚደረገውን የህዝበ ውሳኔው አፈጻጸም በበላይነት ይመራል፤
2. በ6ቱ ዞኖችና በ5ቱ ልዩ ወረዳዎች የምርጫ ጣቢያዎች በአግባቡ መደራጀታቻውን ያረጋግጣል፤
3. ቦርዱ በሚሰጠው የውሳኔ አግባብ መሰረት የምርጫ አስፈጻሚዎችን ይደለድላል ወደ ምርጫ ጣቢያ ያሰማራል፤
4. በ6ቱ ዞኖችና በ5ቱ ልዩ ወረዳዎች ለተቋቋሙ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች መመሪያ ይሰጣል፣ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤
5. ከቦርዱ የሚላኩ የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ወደ ዞን እና ልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች ያሰራጫል፣ወደ መዳረሻቸው መድረሳቸውን ይከታተላል፤
6. ቦርዱ የሚያስተላልፋቸውን የስራ መመሪያዎች ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣ ለቦርዱም ተገቢውን ሪፖርትና መረጃ ያቀርባል፤
7. አስፈላጊ ሲሆን በቦርዱ እውቅና በህዝበ ውሳኔው ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ያደርጋል፣ ይፋዊ መረጃ ይሰጣል፤
8. ህዝበ ውሳኔውን የሚመለከት አጠቃላይ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፤
9. ቦርዱ ባፀደቀው የኦፕሬሽን መመሪያው ላይ የተሰጡትን ሀላፊነቶች ያከናውናል፡፡

**አንቀፅ 11. <u>የዞን እና የልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ተግባርና ሀላፊነት</u>**

የዞን እና የልዩ ወረዳ ህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነት ይኖሩታል

1. በህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ዋና ፅ/ቤት በተወሰነው መሰረት አስፈፃሚዎችን በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ስር ወደሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ማሰማራት፣
2. የምርጫ ቁሳቁስ ከዋና ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ተረክቦ በስሩ ለሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ማሰራጨት፣
3. በዞኑ ወይም በልዩ ወረዳው ስር የሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎችን መቆጣጠር እና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
4. የህዝበ ውሳኔውን ሂደት አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎችን በአዋጁና በመመሪያ ቁጥር 10/2013 ስለ ምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ አካላት የተደነገገውን መሰረት በማድረግ ቅሬታ ሰሚ አካላትን በማዋቀር ማስተናገድ፣
5. በዞኑ ወይም ልዩ ወረዳው ስር ከሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች የመጡ የህዝበ ውሳኔ ምርጫ ውጤቶችን በማዳመር የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን ህዝበ ውሳኔ ውጤት በጊዜያዊነት ማሳወቅ፣
6. የዞኑን ወይም የልዩ ወረዳውን የህዝበ ውሳኔ ውጤት ወደ ህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ዋና ፅ/ቤት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መድረሱን ማረጋገጥ፣
7. ህዝበ ውሳኔውን የሚመለከት ስልጠናዎችን ማስተባበርና መከታተል፣
8. ህዝበ ውሳኔውን ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ሰራዎች ይሰራል፣
9. በኦፕሬሽን መመሪያው ላይ የተሰጡትን ሀላፊነቶች ያከናውናል።

**አንቀፅ 12. <u>የህዝብ ውሳኔ ማስተባበሪያ ማዕከል ተግባርና ሀላፊነት</u>**

1. የህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ማዕከላት በተመረጡ የዞን/ ልዩ ወረዳ ከሶስት እስከ ሰባት ሰው ያሉት ማዕከል በተመረጡ የዞን/ልዩ ወረዳ ማዕከላት ይቋቋማል።
2. የማስተባበሪያ ማዕከሉ ዝርዝር ተግባርና ሀላፊነት በደቡብ ክልል በ6ቱ ዞንና በ5ቱ ልዩ ወረዳዎች ለሚካሄደው ህዝበ ውሳኔ አፈፃፀም ማብራሪያ መመሪያ ላይ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት ተግባራዊ ይሆናል።

**አንቀጽ 13. <u>የምርጫ ጣቢያ ሕዝበ ውሣኔ አስፈፃሚዎች ተግባርና ሀላፊነት</u>**

ሕዝበ ውሣኔ በሚካሄድባቸው ጣቢያዎች የሚመደቡ አስፈፃሚዎች ተግባርና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው፡

1. ከቦርዱ የተላኩ የሕዝበ ውሣኔ ማስፈፀሚያ ሰነድና ቁሳቁሶችን ከዞን እና ልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች ተረክቦ በጥንቃቄ እንዲጠበቁ ማድረግ፤
2. በህዝበ ውሳኔው ለመሳተፍ መስፈርቱን የሚያሟሉ ድምጽ ሰጪዎችን መመዝገብ፤

3. በድምጽ መስጫ ቀን ድምፅ ሰጪው ድምፅ ከመስጠቱ በፊት ስለድምጽ አሰጣጡ ገለጻ መስጠት፤
4. ከጸጥታ አስከባሪዎች ጋር በመመካከር የድምፅ መስጫ ጣቢያው ሥነሥርዓት መከበሩን ማረጋገጥ፤
5. ድምፅ መስጠቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጠራው በአግባቡ እንዲከናወን ማድረግ፤ የቆጠራውን ውጤት መግለፅ እንዳግባብነቱ ለዞን ወይም ልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት በወቅቱ ማድረስ፤
6. ከላይ የተመለከቱት ሁሉንም የህዝበ ውሳኔ አስፈፃሚዎችን ተግባርና ሀላፊነቶች የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የምርጫ ጣቢያ ሀላፊ በመሆን የሚመደበው የምርጫ አስፈፃሚ የድምፅ መስጫ ጣቢያውን ሕዝበ ውሣኔ አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል እንዳግባብነቱ ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት አስፈላጊውን ሪፖርት ያቀርባል፤
7. ቦርዱ ባፀደቀው የኦፕሬሽን መመሪያው ላይ የተቀመጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## አንቀጽ 14. <u>የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች የሥነ ምግባር መርሆዎች</u>

በየትኛውም ደረጃ የሚሰማሩ የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች የሚከተሉት ኃላፊነትና የሥነ ምግባር መርሆዎችን ማክበር አለባቸው፤

1. በህዝበ ውሳኔው የሚሳተፉ ድምጽ ሰጪዎችን በፍጹም ገለልተኝነት ማሰተናገድ፤ ከማናቸውም ሰው ወይም አካል የሚደርስባቸውን ተጽእኖ አለመቀበል እና ህዝበ ውሳኔውን በሕገ_መንግስቱ፣ በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሰረት ማስፈጸም፣
2. የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸም ተግባራቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ አንዱን ወይም ሌላኛውን የህዝበ ውሳኔ ውጤት የሚደግፉ የሚያስመስላቸውን ንግግር ከማድረግ ወይም አስተያየት ከመስጠት ወይም ልብስ ከመልበስ ወይም ማንኛውንም ምልክት ወይም ቀለም ከመያዝ ወይም ከማሳየት መቆጠብ፣
3. ጋዜጠኞች፣ ታዛቢዎችን፣የሰብአዊ መብት ተከታታዩች፣ የጸጥታ አስከባሪዎችን በአዋጁና በቦርዱ መመሪያዎች መሰረት በቅንነት ማስተናገድ፣
4. በህዝበ ውሳኔው ድምጽ ለሚሰጡ ሰዎችም ሆነ ለሌሎች ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ላላቸው ተገልጋዮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜና ያለ መድሎ መስጠት፤
5. አረጋውያን፣ ጨቅላ ህፃናትን የያዙ ሰዎች፣ነፍሰ-ጡሮች፣አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ-ደካሞች እና ሌሎች ማንበብና መጻፈ የማይችሉ ድምጽ ሰጪዎች በተቻለው ሁሉ ድምጽ ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን ምቹ ሁኔታ እንዲያገኙ ተገቢውን ጥረት ማድረግ፣እንደዚህ ያሉ ድምጽ ሰጪዎች በመረጡት ሰው የመታገዝ መብታቸውን ማክበር ፤ ይህንንም መረጃ መስጠት፣
6. በህዝበ ውሳኔው ድምጽ አሰጣጥ ወቅት ድምጽ የሚሰጡ ሰዎች የፈለጉትን አማራጭ መምረጥ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ድምጽ አሰጣጡም በሚስጥር መከናወኑን ማረጋገጥ፣

7. በህዝበ ውሳኔው ሂደት የሚነሱ ቅሬታዎችን በአዋጁ እና ቦርዱ ባወጣው የቅሬታ አቀራረብና አፈታት መመሪያ ቁጥር10/2013 መሰረት በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት በተዋቀረ የቅሬታ አፈታት አደረጃጀት እልባት እንደሚያገኝ ማሳወቅ፣
8. በህዝበ ውሳኔው በድምጽ ሰጪነት ለመመዝገብ፣ ድምጽ ለመስጠት፣ ቅሬታ ለማቅረብ እና የመሳሰሉትን ተግባራት ለማከናወን የተቀመጡ መመዘኛዎችን በተመለከተ በገለልተኝነትና በተገቢው ጊዜ መረጃ መስጠት።

## አንቀጽ 15. <u>የህዝበ ውሳኔ ታዛቢዎች</u>

1. ቦርዱ በቀረበው የህዝበ ውሳኔ ጥያቄ ላይ የሚደረገውን ህዝበ ውሳኔ ምርጫ አፈጻጸም ለመታዘብ ለሚፈልጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በአዋጁና አግባብነት ባለው የቦርዱ መመሪያ መሰረት ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፤
2. በ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫውን ለመታዘብ አመልክተው ፈቃድ የተሰጣቸውና የመታዘበ ስራውን ሰርተው ሪፖርት ያቀረቡትን አገር በቀል ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቀደም ሲል በተሰጣቸው ፈቃድ አማካይነት ህዝበ ውሳኔውን መታዘብ የሚችሉበትን ሁኔታ ቦርዱ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፤
3. በዚህ መመሪያ መሰረት ህዝበ ውሳኔውን ለመታዘብ ፈቃድ የሚሰጣቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና ወኪሎቻቸው በአዋጁና አግባብነት ያላቸውን የቦርዱ መመሪያዎች ላይ የተመለከቱትን ስለአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች መብትና ግዴታዎች እና ስነ ምግባር ደንብ ድንጋጌዎችን ማክበር አለባቸው።

## አንቀፅ 16. <u>የሰብአዊ መብት ተከታታዩች</u>

ቦርዱ የሰብአዊ መብት ተከታታዩች ተግባር፣ ሀላፊነትና ስነምግባርን በተመለከተ ከሰብአዊ መብት ኮሚሽን ጋር በፈረመው የመግባቢያና የማስፈፅሚያ ሰነዶች እንደ አግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## አንቀጽ 17. <u>ስለ ጋዜጠኞችና መገናኛ ብዙኃን</u>

የህዝበ ውሳኔውን ሂደት መዘገብ የሚፈልግ ጋዜጠኛና መገናኛ ብዙሃኃን በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው የመገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባርና አሰራር መመሪያ ቁጥር 2 /2012 እንደ አግባብነቱ ለዚህ መመሪያም አፈጻጸም ተፈጻሚ ይሆናል።

## ምዕራፍ አራት

## የህዝበ ውሳኔ መራጮች ምዝገባና የመራጮች ትምህርት

### አንቀፅ 18. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች

ማንኛዋም በመራጭነት ለመመዝገብ የምትፈልግ ሰው በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 18 እና በርዱ ባወጣው የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 6/2013 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባታል። አዋጁና የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያው ለዚህ ጉዳይም ተፈጻሚ ይሆናሉ። በአዋጁና በመመሪያው ላይ የተቀመጠው የ6 ወር የነዋሪነት መስፈርት ለህዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ሲባል ህዝበ ውሳኔው በሚካሄድበት ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ለ6 ወራት የኖረች ማለት ነው።

### አንቀጽ 19. የአመዘጋገብ ሥርዓት

1. የህዝበ ውሳኔ  የአመዘጋገብ ሥርዓት በተመለከተ ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ በርዱ ያወጣው የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 6/2013 እና የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ ይፈጸማሉ።
2. በርዱ ለህዝበ ውሳኔ መራጮች ምዝገባ ለብቻው የተለየ የመራጮች መዝገብ ያዘጋጃል። የመራጮች መዝገብ የፆታ እና አካል ጉዳተኝነት የሚመዘገቡበት አምድ ይኖረዋል፤
3. የህዝበ ውሳኔ መራጮች ምዝገባን በሚመለከት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በዞን ወይም ልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ደረጃ ለሚዋቀሩ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ቀርበው መፍትሔ ያገኛሉ፤
4. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ማስተባበሪያ ፅ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ውሳኔው በደረሰው በአምስት ቀን ውስጥ ይግባኙን ለበርዱ ማቅረብ ይችላል፤
5. በበርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማናቸውም ቅሬታ አቅራቢ ይግባኙን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት በአስር ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል።

### አንቀጽ. 20. የምዝገባ ቦታ

1. የሕዝበ ውሣኔ ድምፅ ሰጪ ምዝገባ ቦታ ለህዝበ ውሳኔ የቀረበውን ጥያቄ ባቀረበው ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ውስጥ በርዱ በሚያደራጀው ምርጫ ጣቢያ ይሆናል፤
2. የሕዝበ ውሣኔ መራጮች ምዝገባ በርዱ ከወሰነው የምርጫ ጣቢያ ውጪ በማንኛውም ቦታ ሊካሄድ አይችልም፤

3. የመራጮች ምዝገባ የሚካሄድባቸው ቦታዎች የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ15 ቀናት አስቀድሞ ለህዝብ ይፋ መደረግ አለባቸው፤
4. በአንድ የህዝበ ውሳኔ ምርጫ ጣቢያ የሚስተናገደው የመራጮች ብዛት በመራጮች ምዝገባ መመሪያ ላይ ከተቀመጠው 1,500 ሰው መብለጥ የለበትም፤
5. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን ሊለዋውጥ ይችላል፡፡ለውጡንም የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ5 ቀናት በፊት ለመራጩ ህዝብና ለባለድርሻ አካላት፣ ለታዛቢዎችና፣ ለጋዜጠኞችና ለሰብአዊ መብት ተከታታዩች ይፋ ማድረግ አለበት፤
6. እያንዳንዱ የህዝበ ውሳኔ ምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፤
7. ለህዝበ ውሳኔው አፈጻጸም ልዩ የምርጫ ጣቢያ ማቋቋም አስፈላጊነት ላይ ቦርዱ እንደአግባብነቱ ይወስናል፡፡ ልዩ የምርጫ ጣቢያ ለሚያስፈልጋቸው የህዝበ ውሳኔ መራጮች ቦርዱ ያወጣው የልዩ ምርጫ ጣቢያ አደረጃጀት መመሪያ እንደ አግባብነቱ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ተፈጻሚ ይሆናል፤
8. የህዝበ ውሳኔ መራጮች ምዝገባ የሚካሄድበት ቦታ በተቻለ መጠን ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን እና ነፍሰ ጡር ሴቶች ምቹ ሊሆን ይገባል፡፡

## **አንቀጽ 21. <u>የመራጮች የምዝገባ ቦታ በመሆን የማያገለግሉ ቦታዎች</u>**

ከላይ በአንቀፅ 20/7 ላይ ልዩ ምርጫ ጣቢያ መመስረትን በሚመለከት የተደነገገው እንደተጠበቀ የሚከተሉት ቦታዎች መደበኛ የመራጮች ምዝገባ ቦታ ሊቋቋምባቸው አይችሉም

1. ወታደራዊ ካምፖች
2. ፖሊስ ጣቢያዎች
3. አብያተ ክርስቲያናት
4. መስጊዶች
5. ሌሎች የእምነት ቦታዎች
6. ሆስፒታሎችና በየደረጃው ያሉ የህክምና ተቋማት
7. ሆቴሎች፣ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች
8. የፖለቲካ ወይም የሀይማኖት ድርጅቶች ህንጻዎች እና
9. የግል መኖሪያ ቤቶች

ቦርዱ ያወጣው የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 6/2013 እና አዋጁ እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## **አንቀፅ 22. <u>በመራጮች ምዝገባ ቦታ መገኘት ስለሚችሉ ሰዎች</u>**

1. በመራጮች ምዝገባ ቀናት የሚከተሉት ሰዎች በምርጫ ጣቢያው መገኘት ይችላሉ፤

   ሀ. በቦርዱ እውቅና የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች፣

   ለ. በቦርዱ እውቅና የተሰጣቸው የመገናኛ ብዙኃን አባላት፤

ሐ. የሰብአዊ መብት ተከታታዮች፤

መ. በቦርዱ የተመደቡ እና ማረጋገጫ ያላቸው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰራተኞች፤

ረ. የህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች፤

ሰ. ተመዝጋቢዎች፤

2. ማንኛውም በመራጮች ምዝገባ ወቅት መገኘት ያለበት የምርጫ ታዛቢ ተነግሮት ባይገኝም የመራጮች ምዝገባ ሂደቱ በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይከናወናል::

**አንቀፅ 23. <u>የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ</u>**

1. የህዝበ ውሳኔ ምዝገባ ቦርዱ በሚወስናቸው ቀናት የሚጀመርና የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ ቦርዱ የምዝገባ ቀናቱን ከመወሰኑ በፊት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያማክራል፡፡
2. ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ የሚጀምርበትን ዕለት በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ ከ15 ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች አማካኝነት ለህዝቡ ይገልፃል፤
3. የመራጮች ምዝገባ ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅዳሜ እና እሁድን ጨምሮ በሕግ የተደነገጉ የሕዝብ በዓላትን ሳይጨምር በመንግሥት የሥራ ሰዓት ይከናወናል፡፡

**አንቀፅ 24. <u>ልዩ የምዝገባ ቀን</u>**

1. ከላይ በአንቀጽ 23 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መመዝገብ ያልቻሉ መራጮችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ከመደበኛው የምዝገባ ቀናት በተጨማሪ ልዩ የመራጮች የምዝገባ ቀን ሊወስን ይችላል፡፡

2. ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎችን ዝርዝር በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው የመራጮች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 6/2013 እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 25. የመ<u>ራጮችን መዝገብ ለህዝብ ይፋ ስለማድረግ</u>**

1. የህዝበ ውሳኔው የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ለህዝብ ይፋ ይደረጋል፡፡
2. ማንኛውም ቅሬታ ያለው አካል ለህዝብ ይፋ ከተደረገ በኋላ እስከ አምስት ቀን ድረስ ቅሬታውን ለዞን ወይም ለልዩ ወረዳ ማስተባባሪያ ፅ/ቤት ማቅረብ አለበት

**አንቀፅ 26. <u>የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት</u>**

1. በምርጫ ህጉ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት የቦርዱ ነው፤
2. ቦርዱ መራጮች በቂ የህዝበ ውሳኔ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የመራጮች ትምህርት ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

3. ቦርዱ የመራጮች ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የትምህርት ተቋማት፤ የማስተማር ፈቃድ ይሰጣል፤
4. በ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ የመራጮች ትምህርት ለመስጠት አመልክተው ፈቃድ የተሰጣቸውን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ቀደም ሲል በተሰጣቸው ፈቃድ አማካይነት የመራጮች ትምህርት መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ ቦርዱ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል፤
5. በአዋጁ መሠረት በቦርዱም ሆነ በቦርዱ ፈቃድ በሚሰጣቸው ተቋማትና ድርጅቶች የሚሰጥ ትምህርትና ስልጠና ቦርዱ ከሲቪል ማህበራት ጋር በመመካከር የሚያዘጋጀው የማስተማሪያ ሰነዶችን መሠረት ያደረገ ይሆናል፤
6. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቦርዱ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሰረት ፈቃድ ከተሰጣቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና ተቋማት ጋር በመተባበር የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
7. ማንኛውም ሰው ያለቦርዱ ፈቃድ የመራጮች ትምህርትና መረጃ መስጠት አይችልም። ያለ ፈቃድ የመራጮች ትምህርት በሚሰጥ ማንኛውም ሰው ላይ እንዲሁም ሌሎች ከመራጮች ትምህርት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና የስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 04/2012 ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ አምስት

## <u>የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች፣ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ሥርጭት፣ ርክክብና አያያዝ</u>

### አንቀጽ 27. <u>የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች</u>

ቦርዱ ያወጣቸው የመራጮች ምዝገባ፣የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ እንዲሁም የምርጫ ቁሳቁሶች፣መሳሪያዎችና ሰነዶች ስርጭት፣ርክክብና አያያዝ መመሪያ ቁጥር8/2013 ላይ የተዘረዘሩት የምርጫ ቁሳቁሶች፣መሳሪያዎችና ሰነዶች እንደ የአግባብነቱ የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ መሳሪያዎች፣ ሰነዶችና ቁሳቁሶች በመሆንም ያገለግላሉ።

### አንቀጽ 28. <u>የህዝበ ውሳኔ ማስፈጸሚያ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ሥርጭት፣ ርክክብና አያያዝ</u>

ቦርዱ የምርጫ ቁሳቁሶችና ሰነዶች ስርጭት፣ርክክብ፣አያያዝ እና አወጋገድን አስመልክቶ ያወጣው መመሪያ ቁጥር 8/2013 እና የአዋጁ ድንጋጌዎች ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ ስድስት

## <u>የህዝበ ውሳኔ ክርክር/ውይይት ፣የህዝበ ውሳኔ ሀሳብ እና ምልክቶች</u>

### አንቀጽ 29. <u>የህዝበ ውሳኔ ክርክር/ውይይት</u>

1. የህዝበ ውሳኔ ክርክር ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ እንዲሁም በሚወስነው አይነት እና ይዘት መሰረት ይከናወናል፤

2. የህዝበ ውሳኔ እንዲካሄድባቸው የቀረቡትን የህዝበ ውሳኔ ሃሳቦች ላይ ክርክር/ ውይይት የሚያደርጉ አካላት ክርክር/ውይይት የሚያከናውኑት በቦርዱ የተቀመጠውን የክርክርና የውይይት አይነት እና ይዘት መሰረት በማድረግ ይሆናል፤

3. የህዝበ ውሳኔ ክርክር/ውይይት እንዲያካሂዱ የተመደቡ ወይም የተፈቀደላቸው ፣ግለሰቦች ወይም አካላት ክርክሩን/ውይይቱን ሲያካሂዱ ቦርዱ ያወጣውን የምርጫ ክርከር/ ውይይት አይነትና ይዘት እንዲሁም የስነ ምግባር መመሪያ ማክበር አለባቸው፤
4. ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ ለህዝበ ውሳኔ ለክርክር/ለውይይት የሚያገለግል የተለየ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤
5. የህዝበ ውሳኔ ክርክር/ውይይት የሚያደርጉ ሰዎችን ቁጥር ቦርዱ እንደ አግባብነቱ ይወስናል፤
6. ቦርዱ ያወጣው የምርጫ ክርክር/ውይይት ስነ ምግባር መመሪያ እንደ አግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፤

**አንቀጽ 30 የህዝበ ውሳኔ የምርጫ ምልክቶች**

1. ቦርዱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7(10) መሰረት የህዝበ ውሳኔ ጥያቄ ያቀረቡት አካላት ላቀረቡት አማራጮች ምልክቶች እንዲያቀርቡ ይጠይቃል፡፡ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ቦርዱ አግባብነት ባለው መመሪያ መሰረት ይመርጣል፤
2. የተመረጡትን የመወዳደሪያ ምልክቶች ቦርዱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፤
3. ስለ ዕጩ ምልክቶች በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው መመሪያ እንደ አግባብነቱ ለህዝበ ውሳኔው አፈጻጸምም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ

**አንቀጽ 31. በሕዝበ ውሣኔው በድምጽ ሰጪነት ስለመሳተፍ**

1. ማንኛውም የሕዝበ ውሣኔ ድምፅ ለመስጠት የሚችልና የማይችል ሰው በተመለከተ በአዋጁ እና ቦርዱ ባወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ አፈጻጸም መመሪያ ላይ የተደነገጉት መስፈርቶች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በተለያየ ምክንያት በተመዘገቡበት ምርጫ ጣቢያ በምርጫው እለት መምረጥ ለማይችሉ መራጮች ድምፅ መስጠት የሚያስችላቸውን ልዩ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤
3. በንዑስ ቁጥር 2 ላይ በተመለከተው መሰረት የሚሰጥ ውሳኔ ቦርዱ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡ በዚሁ ስርዓት ድምፅ የሚሰጥበትን የጊዜ ገደብ ይፋዊ መግለጫው ውስጥ የሚካተት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 32. <u>የሕዝበ ውሣኔ ድምጽ መስጫ የጊዜ ሰሌዳ</u>**

1. የሕዝበ ውሣኔው ድምፅ መስጫ እና ውጤቶች ይፋ ማድረጊያ ጊዜ ቦርዱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተመካክሮ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይወሰናል፤
2. ከላይ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ቦርዱ የተለየ የድምጽ መስጫ ቀን ሊወስን ይችላል፤
3. ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በተመለከት ቦርዱ ባወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 33. <u>የሕዝበ ውሣኔ አማራጮችን ስለማስተዋወቅ</u>**

1. ቦርዱ የህዝብ ውሳኔውን ጥያቄ እና ያሉትን አማራጮች በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7(9) መሰረት ለማንኛውም መራጭ ግልፅ በሆነና የመራጮች ሀሳብና ፍላጎት ገላጭ በሆነ ሁኔታ በፅሁፍ ያሰፍራል።
2. ቦርዱ ለህዝበ ውሳኔ የቀረቡትን የህዝበ ውሳኔ አማራጭ ሀሳቦች እና የሚወከሉባቸውን ምልክቶች ከወሰነ በኋላ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።

**አንቀጽ 34. <u>ስለ ድምፅ መስጫ ወረቀት</u>**

1. የሕዝበ ውሣኔ ድምፅ የሚሰጥበት የውሳኔ ሃሳብና ሃሳቡን እንዲወክል የተመረጠው የመወዳደሪያ ምልክት ለዚህ በተዘጋጀ የድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ መታተም ይኖርበታል፤
2. የእያንዳንዱ የድምፅ መስጫ ወረቀት የወረቀት ጥራት፣ ቅርፅ፣ ቀለም፣ ብዛት ወይም ይዘት አስቀድሞ በቦርዱ የሚወሰን ይሆናል፤
3. የህዝበ ውሳኔ ሃሳቡን የሚወክሉት ምልክቶች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚታተሙበትን ቅደም ተከተል ቦርዱ ባለድርሻ አካላት እና ታዛቢዎች በተገኙበት በዕጣ ይወስናል።

**አንቀጽ 35. <u>አንድ ቦታ ብቻ ድምፅ ስለመስጠት</u>**

1. በሕዝበ ውሣኔው ድምፅ የሚሰጥ ሰው በተመዘገበበት በአንድ ቦታ ብቻ ድምፅ መስጠት አለበት፤
2. ከአንድ ቦታ በላይ በድምፅ ሰጪነት ተመዝግቦ ወይም ከተመዘገበበት ቦታ ውጪ ድምፅ ሲሰጥ የተገኘ ሰው እየሰጠ እጁ ላይ የተያዘው ድምጽ በድምጽ ቆጣሪዎች ውድቅ ይደረጋል። አግባብነት ባለው ሕግም ይጠየቃል፤
3. ቦርዱ ያወጣቸው የመራጮች ምዝገባና የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ እንደአግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 36. <u>የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት</u>**

1. የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ዕለት ከመድረሱ 3 ቀን በፊት ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በምርጫ ጣቢያ ህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች መዘጋጀት አለባቸው፤
2. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የድምጽ መስጫ ጣቢያውን ደህንነት የማስጠበቅ ሀላፊነት አለበት፤
3. የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት በርዱ ባወጣው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራርና የሥነ ምግባር መመሪያ መሰረት እንዲጠበቅ ይደረጋል፤
4. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሚመለከተውን አካል በመጠየቅ የድምጽ መስጫ ጣቢያውንና የአካባቢውን ፀጥታና ደህንነት የሚያስከብሩ የፖሊስ ወይም የፀጥታ አስከባሪዎች ቦርዱ ባወጣው የምርጫ ማስፈጸሚያ ተቋማት ጸጥታ አስከባሪዎች የአሰራርና የሥነ ምግባር መመሪያ መሰረት እንዲመደቡለት ያደርጋል።
5. የድምጽ መስጫ ቀን የድምጽ መስጫ ጣቢያው ከመከፈቱም ሆነ ድምጽ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጋ በኃላ ከህዝበ ውሳኔ አስፈጻሚዎች፣ ከታዛቢዎች፣ የሰብአዊ መብት ተከታታዩች ፣ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፤
6. ቦርዱ ያወጣቸው ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መመሪያዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 37. <u>የህዝበ ውሳኔ ፀጥታ አስከባሪዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ቦርዱ ያወጣው የምርጫ የጸጥታ አስከባሪዎች የሥነ ምግባርና የአሰራር መመሪያ እንደ አግባብነቱ ለህዝበ ውሳኔ አፈጻጸምም ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 38. <u>የድምጽ መስጫ ሰዓት</u>**

1. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የህዝበ ውሳኔው የድምጽ መስጫ ሰዓት ከማለዳው 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ድረስ ነው።
2. ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የህዝበ ውሳኔ ምርጫውን ነፃና ፍትሀዊነት ይበልጥ ያረጋግጣል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰዓቱ እንዲራዘም ሊያደርግ ይችላል።
3. ቦርዱ የድምጽ መስጫ ሰዓቱን በተለየ ሁኔታ የወሰነ እንደሆነ የተወሰነውን የድምጽ መስጫ ሰዓት ድምጽ ሰጪዎች በይፋ እንዲያውቁት ያደረጋል።

**አንቀጽ 39. <u>ድጋፍ ስለሚፈልጉ ድምጽ ሰጪዎች</u>**

አዋጁና ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 40. <u>ድምፅ ስለመስጠት</u>**

አዋጁና ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 41. <u>ስለተበላሸ የድምፅ መስጫ ወረቀት</u>**

አዋጁና ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 42. <u>የተሰጠ ድምፅ ውድቅ ስለሚሆንበት ሁኔታ</u>**

ማንኛውም ድምፅ ሰጪ የሰጠው ድምጽ ዋጋ አልባ የሚሆነው፡-

1. በድምፅ መስጫ ወረቀቱ ላይ ከተሰጡ አማራጮች ምንም ካልመረጠ፣
2. ሁለቱንም አማራጮች ከመረጠ፣
3. ድምጽ የሰጠበት የድምጽ መስጫ ወረቀቱ በቦርዱ ያልተዘጋጀ ወይም የቦርዱ ህጋዊ ማህተም የሌለው ከሆነ፣
4. የትኛውን ምልክት (አማራጭ) እንደመረጠ በማያመለክት ሁኔታ ድምጽ ከሰጠ
5. ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀፅ 43. <u>ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ</u>**

የድምጽ መስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑና የሚቋረጥበት ሁኔታ ቢፈጠር ስለሚወሰዱእርምጃዎች ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀፅ 44. <u>ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም</u>**

ድምጽ መስጠትን ለመቃወም ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀፅ 45. <u>ስለጊዜያዊ ድምፅ</u>**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 46. <u>በድምፅ መስጫ ዕለት ስለሚገኙ ሰዎች</u>**

1. በድምፅ መስጫ ዕለት የድምፅ መስጫ ጣቢያ መገኘት ያለባቸው አካላት፡-

   ሀ/ የህዝበ ውሳኔ ምርጫ አስፈፃሚዎች፣

   ለ/ የሰብአዊ መብት ተከታታዩች

   ሐ/  ታዛቢዎች

2. ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ለመራጭነት የተመዘገቡ መራጮች እንዲሁም ከቦርዱ ፍቃድ ያገኙ የመገናኛ ብዙኃን በምርጫ ጣቢያው ሊገኙ ይችላሉ።

## ምዕራፍ ስምንት

## ስለድምፅ አሰጣጥ መጠናቀቅ

**አንቀፅ 47. የምርጫ ጣቢያ መዘጋት**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 48. የድምፅ መስጫ ሳጥን ስለመቆለፍ እና ስለሚደረግ ጥንቃቄ**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 49. ስለድምፅ ቆጠራው አፈፃፀም ገለፃ ስለመስጠት**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀፅ 50. የድምፅ መቁጠሪያ ሰነድ እና ቁሳቁስ ስለማዘጋጀት**

ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ለቆጠራው ተግባር የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶችን ቦርዱ ባወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ መሰረት ዝግጁ ማድረግ አለበት።

**አንቀጽ 51. የድምጽ ቆጠራ፣ ማዳመርና ውጤት አገላለጽ**

የድምጽ ቆጠራ፣ማዳመርና ውጤት አገላለጽ ሥራዎች ቦርዱ ባወጣው የድምጽ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ መሰረት ይከናወናል።

**አንቀፅ 52. የውጤት ማመሳከሪያውን በግልጽ ስለማሳየትና ስለማሸግ**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ ቆጠራ፣ማዳመርና ውጤት አገላለጽ መመሪያ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 53. የድምፅ ቆጠራ ውጤትና የምርጫ ቁሳቁስ ስለመላክ**

ቦርዱ ያወጣው የድምጽ ቆጠራ፣ማደመርና ውጤት አገላለጽ መመሪያ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀፅ 54. በድምፅ አሰጣጥ፣ቆጠራና ውጤት አገላለጽ ሂደት ስለሚቀርብ ቅሬታ**

1. በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራ፣ ማዳመር እና ውጤት አገላለፅ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በተዘረዘረው እንዲሁም ቦርዱ ባወጣው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 10/2013 ዓ.ም መሰረት በዞንና በልዩ ወረዳ ደረጃ በሚዋቀሩ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ውሣኔ ያገኛሉ።

2. የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ሀላፊዎች ለጽሕፈት ቤታቸው የቀረቡ ቅሬታዎችና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ ውሣኔዎችን ዋና ቅጂ እና የፅሑፍ ማስረጃዎችን ፋይል አድርገው መያዝ አለባቸው።
3. በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ህዝበ ውሳኔ ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማናቸውም ሰው ውሳኔ በደረሰው በ5 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለቦርዱ ዋና ፅ/ቤት ማቅረብ ይችላል፤
4. በቦርዱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማናቸውም ሰው ይግባኙን ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡

## አንቀፅ 55. <u>አሸናፊውን የህዝበ ውሳኔ ሀሳብ ለመለየት ያልተቻለ እንደሆነ</u>

1. ውጤቶች ከተደመረና ቅሬታዎች እልባት ካገኙ በኋላ የህዝበ ውሳኔ ሀሳቦቹ እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አብላጫ ድምፅ ያገኘውን የህዝበ ውሳኔ ሀሳብ ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ ቦርዱ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ ይካሄዳል።
2. ድጋሚ ህዝበ ውሳኔ ማድረግ የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር ቦርዱ ያወጣው የድጋሚ ምርጫ መመሪያ እና ሌሎች መመሪያዎች እንደ አግባብነታቸው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## አንቀፅ 56. <u>በቦርዱ ስለሚገለፅ የህዝበ ውሳኔ ውጤቶች</u>

1. ቦርዱ የህዝበ ውሳኔ ውጤቶች ተጠቃለው እስከሚደርሰው ድረስ የመጣለትን የዞን ወይም የልዩ ወረዳ ምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይፋ ያደርጋል።
2. ቦርዱ ከ6ቱ ዞኖችና ከ5ቱ ልዩ ወረዳዎች የህዝበ ውሳኔ ውጤቶች ሲደርሱት የዞኖቹንና የልዩ ወረዳዎቹን ካረጋገጠ በሁዋላ የህዝበ ውሳኔ ውጤቶችን ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።

## አንቀፅ 57. <u>በቦርዱ ስለሚሰጥ ይፋዊ መግለጫ</u>

1. የህዝበ ውሳኔው ሂደት ተጠናቆ አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰባሰቡ በኋላ ቦርዱ በጊዜ ሰሌዳው መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል።

ሀ. በህዝበ ውሳኔው በእያንዳንዱ ዞንና ልዩ ወረዳ የተመዘገቡ መራጮች ብዛት፣

ለ. በህዝበ ውሳኔው በእያንዳንዱ ዞንና ልዩ ወረዳ ድምፅ የሰጡ መራጮች ብዛት፣

ሐ. በህዝበ ውሳኔው በእያንዳንዱ ዞንና ልዩ ወረዳ ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች በመቶኛ፣

መ. ለምርጫ የቀረቡት የህዝበ ውሳኔ ሃሳቦች፣

ሠ. በ6ቱ ዞኖች እና ከ5ቱ ልዩ ወረዳዎች አብላጭ ድምፅ ያገኘው የህዝበ ውሳኔ ሃሳብ፣

ረ. በህዝብ ውሳኔ በእያንዳንዱ ዞንና ልዩ ወረዳ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ከጥቅም ውጭ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት ይፋ ያረጋል:

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 58. በጀት**

ቦርዱ ለህዝበ ውሳኔ ምርጫ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን በጀት ከመንግስት ያስፈቅዳል።

**አንቀጽ 59. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም አካል የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡

**አንቀጽ 60. ስለቅጣት**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ከጣሰ ወይም ሆን ብሎ የህዝበ ውሳኔውን ሂደት የሚያሰናክል ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ይጠየቃል።

**አንቀጽ 61. ተጨማሪ ህጎችና መመሪያዎች**

ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል ቦርዱ ያወጣቸው የተለያዩ የምርጫ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች እንደአግባብነታቸው በህዝበ ውሳኔ አፈጻጸም ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 62. ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና አሰራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

**አንቀጽ 63. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከጸደቀበት ከጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
ሰብሳቢ